# ሕዝባችንን ከቀጣዩ የዘር ማጽዳት ጭፍጨፋ እንታደገው

ሚያዝያ 1 ቀን 2012 ዓ/ምህረት

ቀሲስ አስተርአየ

nigatuasteraye@gmail.com

ወያኔወች በሰነዘሩት የዘር ማጥፊያ ሁላችንም እኩል እየተሰበርን ባንጠፋም ቢያንስ ባንዱ ወይም በሁለቱ ሳይሰበር ያመለጠ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ያለ አይመስለኝም።

ወያኔዎች በኢትዮጵያ የተወለደውን ሁሉ በማንነቱ ሰብረው ኢትዮጵያን አጥፍተው ለዘላለም ለመግዛት በዘረጉት እቅድ፤ ከመጀመሪያ ጀምረው አማራውንና ኦርቶዶክሱን ሰበርነው እያሉ እንደመጡና ስኪሞቱ ድረስ በተግባር እንደፈጸሙትም ግልጽ ነው። አሁንም ቀርጸው በተውልን ህገ መንግስትና በወራሾቻቸው ግፉ እንደደቀጠለ ነው።

ወያኔወች በአራቱ ማንነቶች ላይ የሚፈጸሙትን የዘር ማጥፋት ስልቶች hard soft law እያለ በ Central America በኢራክ፤ በቦስንያ ፤ በኮሶቮ፤ በሶማሊያ፤ በረዋንዳ፤ በቡርንዲ፤ በኮንጎ፤ በሌሎችም ባልጠቀስኳቸው አገሮች ላይ የተፈጸመው የዘር ማጥፋት መስፈርት ዓለም ከመለካቱ በፊት የኛ አባቶች ከዚህ በታች በምጠቅሳቸው መስፈርቶች ሰፍረው ሰጥተውን ነበር።

1ኛ፡- በመሬት ያለውን ተፈጥሮ አብጁ የሚለውን መሠረት በማድረግ ያለበቂ ምክንያት ከቤተ ክርስቲያን አጸድ አንዲት ቅጠል መቁረጥ የተወገዘ ነው ብለው ነግረውናል

2ኛ፡-አውናን ዘር እንዳይተካ ባደረገው ስህተት የደረሰበትን መቅሰፍት መነሻ በማድረግ ዘር መድፋት ክልክል ነው ብለው ነግረውናል።

3ኛ፡-ቅዱስ አትናቴወስ “አምላክ ዘርን ካባቱ ወገብ ወደናቱ ማህጸን ቀድቶ በናቱ ማህጸን በሰፋድል ጠቅልሎ የህይወት መንፈስ አሳድሮ በ40 ” ያለውንም መሰረት በማድረግ ጽንስን ማስወረድ ክልክል እንደሆነ ነግረውን ነበር።

4ኛ፡- ሰው የአምላክ አርአያ ነው የሚለውን መሠረት በማድረግ አንድ ሰው መግደል የሚመስለውን ሁሉ መግደል ነውና ነው የሚያስከትለው ፍዳ በሟቹ ብቻ የሚገታ አይደለም ብለው አስተምረውን ነበር።

ከእነዚህ ጥፋቶች  አንዱን የፈጸመ ሰው ያካባቢው ሸንጎ ወይም ቀኖናው የሚጠይቀውን ፍዳ ሳይከፍል ከህብረተ ሰብ ጋራ ማህበራዊ ተሳትፎ ሊኖረው ቀርቶ እሳት አይጫጫርም ነበር።

በህዝባችን ላይ የሚካሄደው የዘር ማጥፋቱ አባቶቻችን እና ዓለም አቀፍ ሊቃውንት ከሰፈሩት መስፈርት አልፎ ተርፎ ልንገልጸው ካቅማችን በላይ የሆነ የአረመኔ የዘር ጭፍጨፋ

ከዚህ በታች በተዘረዘሩት በአራት አቅጣጫወች በጠቅላላው ህዝባችን ላይ እየተካሄደ ነው።

1ኛ፡-በሰውነት

2ኛ፡-በኢትዮጵያዊነት

3ኛ፡-በኦርቶዶክስነት

4ኛ፡-በአማራነት

ከ4ቱ ማንነቶች ባንዱ ወይም በሁለቱና  በሶስቱ ማንነቶቹ ላይ የዘር ጥፋት ዘመቻ ሲፈጸም፤ አራቱንም ይዞ በተገኘው በአማራው ህብረተ ሰብ ላይ ግን እጅግ በጣም እጅግ  በከፋ ግድያና መታረድ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ተፈጽሞበታል። አሁንም እየተፈጸመበት ነው።

አባቶቻችን መስፈርቱን ለክተው ካስቀመጡልን ጋራ በኢራክ፤  በቦስንያ ፤ በኮሶቮ፤ በሶማሊያ፤ በረዋንዳ፤ በቡርንዲ፤ በኮንጎና  በሌሎችም  ባልጠቀስኳቸው  አገሮች ላይ በውጭ ወራሪወችና መንግሥት በራሱ ዜጋ ላይ የሚፈጽመው የዘር ማጥፋት የሚሰፍርበት ቢደመር የሚያስከፍለውን ዋጋ በመሬት የነበረ ዛሬም ያለን ወደፊት የሚቀጥለው የሰው ዘር ሊከፍለው የማይችለው ከመሬት ሸክም አቅም በላይ ነው።

ወያኔወች ሲወለዱ ያጠለቁት ጥብቆ  የተሰራበት ዘሀውና ማጉ በኢትዮጵያዊነት ጥላቻ ላይ ስለተመሰረተ ንክኪ ያለውን

ሁሉ እየፈለጉ ጠራርገው ሲያጠፉ፤ አማራውንና ኦርቶዶክሱን ጨርሰው ለማጥፋት የቀረቻቸውን ኃይል እየተጠቀሙ ነው።

በባህላችን ሞትኩ ብሎ ሲመነኩስ በለበሳት አጽፍ ተገንዞ የሚቀበረው መነኩሴ ብቻ ነበር። የቀረው የኔ ቢጤ ሲሞት የሚቀበረው ፤ በሌላ አዲስ ከፈን እንጅ በተወለደበት ጥብቆ ተገንዞ  አይቀበርም ነበር።

በሰይጣን ክፉና ጠማማ ባህርይ ከናቱ ማህጸን ጀምሮ የተወለደበትን ክፉ ባህርያት ሳይለቅ ግፍ ሲፈጽም ኖሮ በሚሞትባት ቅጽበት መላከ ሞት ሲጎበኘው እየተናዘዘ የሚሞተውን ለመግለጽ ”ሲወለድ ያጠለቀውን ጥብቆ ሲሞት አወለቀው“ ብለው ወላጆቻችን ነግረውናል።

ይህ አባባል መላ ህይወቱን ግፍና በደል ፈጽሞ ሊሞት ሲል ንስሀ እየገባ የሞተውን የክፉ ሰውን ባህርይ ለመግለጽ የተናገሩት እንደሆነ ግልጽ ነው።

እንደ ወያኔዎች የተወለደበትን ጥብቆ  ሳያወልቅ ንስሀ ሳይገባ በዚያው በተጠቀለለበት ጥብቆ ራሱን ገንዞ ለሚሞተው ግፈኛና በደለኛ፤ ፍዳውና ግፉ ከመሬት ሸክም አቅም በላይ በመሆኑ ለአረመኔነቱ ለጭካኔው እና በመጨረሻ ለሚሸከመው የግፍ ፍዳ መግለጫ ቃልና ምሳሌ ያጡለት ይመስለኛል።

ወያኔዎች ሲወለዱ ያጠለቁትን ጥብቆ ተገንዘው የተቀበሩበት ቢመስለንም ቅሬቱን ለነሽመልስ አብዲሳን እና

ለነታየ ደንዳ አውረስውት በአርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና ባማራው የሚፈጽሙው የዘር ማጥፋት ዘመቻ በባሰ አስከፊና ዘግናኝ ጭፍጨፋ እየተፈጸመ ነው።

ወያኔወች የግፉ ጽዋው ሞልቱ ወደራሳቸው ሲገለበጥባቸው፡ የግፉን ጽዋ መክፈላቸው የማይቀር ፍዳ መሆኑን ተገንዝበው ንስሀ በመግባት አምላክንም ህዝባቸውንም ይቅርታ መጥየቅ ሲገባቸው በዚያው በመርገም ቁረንጪቻቸው ተግንዘው አማራውንና ኦርቶዶክሱን ሰበርነው እያሉ የፎከሩበትን ቃል ገልብጠው፤ ጠቅላይ ምንስቴር ዓቢይን ከሰበሯቸው ካአማራው ና ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክእርስቲና ጋራ ደምረው ሰበሩን እያሉ በዓለም መድረክ መክሰሳቸው የ <u>**ተባርዮ**</u> ን ስፋትና መጠን እጅግ በጣም ለጠጡት።

<u>**ተባርዮ**</u> የምንላት የብድራት ክፍያ ቃል ባንድ ወቅት ወይም ባንድ ዘመን ግለ ሰብም ሆነ ቡድን፤ በሌላ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ የተፈጸመ በደልና ግፍ፤ ሳይከፈል የማይቀር መሆኑን በሊቃውንት አበው ተደጋግማ ስትነገር የሰማኋት አስፈሪና አስጠንቃቂ ቃል ናት።

በአበው ተደጋግማ ስትነገር የሰማኋት ይህች አስፈሪና አስጠንቃቂ ቃል በሁሉም ተረሳች። ከእኛ ከካህናት ህሊናማ ጭራሽ ተደመሰሰች ።

ይህች ቃል ከዚህ በታች ከምጠቅሳት እግዚአብሔር በነቢዩ በአሞጽ አንደበት ከተናገረው ከቁጣ ትንቢታዊ ንግግር ተመዛ የወጣች ቃል ናት። “እስመ ርኢኩ ብዙኃ ኃጢአተክሙ ወዓቢየ ጌጋየክሙ ፤ ተኃይድዎ ለጻድቅ ወትነሥኡ ቤዛ ። ወታቴክልዎ ለነዳይ በውስተ ሞኅት ። በእንተ ዝንቱ ጠቢብኒ ያረምም ይእተ አሚረ” (አሞ 4፡12)

ይህም፡- “በንጹሐን ላይ የምትፈጽሙት የግፋችሁ ክብደት፤ የብዝበዛችሁ ብዛትና የምታዋክቡት ወከባ ጽዋው ሞልቶ ፍዳችሁን በምትከፍሉበት ወቅት፤ ጥበበኛ አስተዋይ ከመደነቅና ከመገረም በቀር የኔ ሰአትና ድርሻ ነውና ሊቃወምም ሊደግፍም ካቅሙ በላይ ነው” ብሎ እግዚአብሔር በነቢዩ አሞጽ አንደበት የተናገረው ነው።

ያስተማሩን መምህራን አንድም ብለው ሲተረጉሙ፤ መምህሮቻቸው በቅኔያቸው የገለጹትን ካባቶቻቸው የሰሙትንንና በራሳቸው ዘመንም ራሳቸው የተገነዘቡትን ብትንትን አርገው ሲግቱን ቃሉን ብቻ ሳይሆን፤ ከአቋቋማቸው ከድምጻቸውንና ከእንቅስቃሴያቸውና ከሙሉ ስሜታቸው ጋራ በመላ ሰውነታችን ከሚመላለሰው ደማችን ቀላቅለውት ነበር።

(**ተባርዮ**) የምትለው ቃል የተሸከመችው መለኮታዊት ሀሳብ ወያኔወች ከህሊናችን ባያጠፉብን ኑሮ፤ በወያኔወች ላይ በመካሄድ ያለው የእግዚአብሔር ፍርድ መሆኑን ተገንዝበን በአንክሮ ከእንቅልፋችን በነቃን ነበር። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንና አማራው ዘመተብን የሚል የጩኸት

ቅሚያ አጭበርባሪ ክስ ከራሱ ከወያኔ እየሰማን እኛ ካህናቱ አፋችንን አፍነን ባልተቀመጥን ነበር።

ወያኔ ታራሚ እያለ ዘር ማጥፋቱን ሲፈጽም በመንበሩ ላይ ቁጭ ብሎ ሲያስፈጽም የነበረው ማነው? ዛሬ በተጠያቂነት ላይ ያሉትን  ጠቅላይ ምንስተር ዓቢይንስ መልምሎ  አሳድጎ ለዚህ ያደረሳቸው ማነው?ዘሩ በመጥፋት ላይ ያለው አማረውና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ናቸውን?

አምላክ በአምሳሌ ልፍጠር ብሎ በራሱ ወግኖ የፈጠረውን ሰው፤  ወያኔወች ከአምላክ ወገንነቱ ለይተው  ፤ በየወገኑ ተለይቶ እንደ ተፈጠረው እንስሳ አንዱን ካንዱ የፈረጁበትን መንገድ ሳንከተል  “ብጹዕ ቅዱስ  ፓትረያርካችን ከአምላክ በተቀበሉ በረከት  ይባርኩን” የምንላቸውን አቡነ ማትያስን አማራ ናቸው ሊሉ ነውን?

“ፍየል ከመጠበቅ ውጭ  ምን ፋይዳ የሰራል” እያለች የወያኔወች አፈ ቀላጤ ሚሚ ስብሀቱ በአማራው ላይ የተናገረችውን ስላቅ ረስተው፤ ዛሬ ተገልብጠው አማራው ዘራችን አጠፋው  ሲሉ   ዓለም ይታዘበናልና ዝም በሉ የሚል አንድ መንፈሳዊ አስተዋይ መካሪ ከመካከላቸው እንዴት ይጥፋ!

አሁን የሚጠጡትን የግፍ ጽዋ ያመጣባቸው ለ28 አመታት በአማራው ላይ ሲናገሩት የነበረው ስላቅ መሆኑን

ተገንዝበው የራሳቸውን ህሊና መታዘብ በተጋባቸው ነበር።
“እስመ በ ጻድቃን ዘይበጽህ ላእሌሆሙ ግብረ ረሲአን” (
መክ 8፡14 ) ማለትም፡- ”ለኃጣን የወረደ መቅሰፍት ለጻድቃን ይተርፋል“ የሚለውን እየጠቀሱ ባንደበታቸው ግፍ የተናገሩትን በእጃቸው ብዙ ደም ያፈሰሱትን እነ ደብረጽዮንን ዘውድ ከማቀዳጀት ይልቅ ቀድም ብለው ቢገስጹ ኖሮ እነሱም እኛም አሁን ከገባንበት አዘቅት አንገባም ነበር።

**“ኦርቶዶክሱንና አማራውን ሰበርነው እርቅ የሚሉ ሁሉ ይገደሉ”** ያሉትን እነ አቶ ስብሀት ነጋንና እና እነ ስዩም መስፍንን ከቅዱስ ጳውሎስ ጋራ እያወዳደሩ በሰማይ የክብር አክሊል እንደሚጠብቃቸው እያደረጉ ማቅረባቸው፤ እነ አቶ ስብሀት ነጋ ከፈጸሙት ሁሉ ግፍ የሚከብድ የሚዘገንን ግፍ ፈጸሙ። ተባርዮን ከማያስቀረው ከእግዚአብሄር ጋራም ክፉኛ ተጋጩ።

አውቀን በድፍረት፤ ሳናውቅ በስህተት ሁላችንም በድለናልና ይቅር እንባባል ማለት ሲገባቸው፤ አማራውና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን ከጠቅላይ ምንስቴር ዓቢይ ጋራ ደምረው መክሰሳቸው ለጅልጅ የሚተላለፍ በስንክሳራችን የሚመዘገብ ስህተት ሰሩ።

ስህተት ሰሩ ስል፤ የኛን ልቅሶ ሊጋሩን ይቅርና ልቅሶአችንን በዘፈናቸው አፈኑት ለመለት እንጅ፤ የትግራይ ህዝብ ሲገደል በማልቀሳቸው አይደለም። ሲገደል ለኖረው

ለወገናቸው ለአማረው ሞት ከኛ ጋራ ባለማልቀሳቸው እርም እንደበሉ፤ ወገናችን የትግራይ ህዝብ ሲገደል አብረናቸው እንዳናለቅስ በማድረጋቸው እኛንም እርም አበሉን።

አማራውንና የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ከዓቢይ ጋራ ጨፍልቀው ገደሉን እያሉ በመክሰሳቸው፤ የኛን ልቅሶ በዘፈናቸው ሲያፍኑ በመኖራቸውና በወገናችን በትግራይ ላይ የደረሰውን ሀዘን እንዳንካፈል በማድረጋቸው እንውቀሳቸው እንጅ፤ 28 ዓመት ሙሉ ስናለቅስ ፖለቲካ ገባችሁ እያሉ ከተሳለቁብን አስመሳይ ቄሶችና ሰባኪወች፤ ለወገኖቻቸው በማልቀስ ላይ ያሉት የትግራይ ወገኖቻችን ካህናት ይሻላሉ።

ለ28 ዓመት ፖለቲካ አንገባም ትሉ የነበራችሁ፤ ዛሬ በወገኖቻቸው ሞት በሚያለቅሱት በውገኖቻችን የትግራይ ካህናት ላይ በር የምትዘጉና በሀዘናቸው ላይ የምትሳለቁ ካላችሁ ከቤተ ክርስቲናችን አስተምህሮ የራቃችሁ ናችሁ።

እኛ ባለቀስንበት ጊዜ የትግራይ ካህናት ከኛ ጋራ ባለመልቀሳቸው የምንወቅሳቸው ከሆነ ፤ እኛም ከነሱ ጋራ ጋራ ካላለቅሰን ተጠያቂወች ነን። ቀድሞም ከኛ ጋራ ያላላቀሳችሁና ዛሬም ከትግራይ ካህናት ጋራ ያላለቀሳችሁ ከሁላችንም ባለመሆናችሁ ከዚህ በታች በምገልጸው በቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ የተወገዛችሁ ናችሁ።

## <u>የቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ</u>

ሌላውን ሁሉ እንለፈውና በነነዌ ላይ የተቃጣውን መቅሰፍት አምላክ በምህረቱ በመመለሱ ለተከፋው ለነቢዩ ዮናስ "ኢይምህካኑ ለነነዌ ሀገር ዓባይ ዘሀለው ውስቴታ ሰብእ ፈድፋደ ዘይበዝሁ እም አሰርቱ ወክሌቱ ዕልፍ እለ ኢፈለጡ ጸጋሞሙ ወየማኖሙ" (ዮናስ 4፥11) ሲል የተናገረው እንዴት ማስታወስ ተሳናችሁ? ይህም ማለት፡- ግራና ቀኛቸውን ገና ለይተው ያላወቁ ከ 12 ዕልፍ በላይ የሰፈረባት ታላቋ አገር ነነዌ ታሳዝነኛለች። እንዳለው፡- ከቁጥር ቀመር ባላይ ያሉት ገና ግራና ቀኝ እጃቻቸውን ለይተው ያላወቁ ዕልፍ የኢትዮጵያ ህጻናት ሲጨፈጨፉ ትላንትም ዛሬም ዝም ማለታችሁ አያስወግዛችሁምን?

በሊጦኑ "አድኅን ዛተኒ ሀገረ ወካልእታኒ አህጉሩ ወበህውርተ" እያልን እንድንጸልይ። በቅዳሴያችንም " ወዛቲ ሀገር ወኲሎን አህጉር ወበህውርት ወደሰያት ወአእጻዳት ወምኔታት " ባስልዮስ ቁጥ 54" እያልን ማለትም፡- ህችን አገር ኢትዮጵያን፤ ጎረቤቶችንና ሌሎችንም አጎራባች አገሮች ከወራሪ አድናቸው የሚለውን በድግምት ብቻ ሳይሆን በተግባር እንድናውለው ቤተ ክርስቲያናችን አስተምራን አልነበረምን?

አባቶቻችን ኢትዮጵያን በዓለም ታሪክ ልዩ ያደረጌት ለጎረቤት አገሮችም ለምሳሌነት ያበቋት ቅዳሴውን ሊጦኑን (liturgy) በተግባር በመተርጎማቸው ነበር።

ከውጭ ወራሪ ሲመጣ አ ዘኢትፈቅድ ዘኃጥአ ሞተ አላ ግብአተ። አ ዘታወጽአ ለሕጻን እምሐቄ ብእሲ ወትፌንዎ ውስተ ከርሠ ብእሲት ወትጠበልሎ በሰፋድል ረቂቅ

ወእንዘ ማይ ታረግእ በጥበብከ ወትነፍህ ላዕሌሁ መንፈሰ ህይወት ወበአርባ እለት ትሰይሞ ” ቁ 113።

ምንም ያላወቁ ህጻናት መጨፍጨፍ ቀርቶ ለሞት የሚየበቃ በደል ከወገን መካከል የፈጸመ ቢኖር ተጸጽቶ ንስሀ እንዲገባ እንጅ ለሞት እንዳይዳረግ የመከላከል ሀለፊነት ነበረብን።

አምላክ ዘርን ካባቱ ወገብ ወደናቱ ማህጸን ቀድቶ በናቱ ማህጸን በሰፋድል ጠቅልሎ የህይወት መንፈስ አሳድሮ በ40 ቀኑም የሰየመውን ጽንስ ማስወርድንም እንድንከላከል አስተምራን ነበር። በዚህ ሁሉ ሀላፊነታችን ባለመወጣትችን በኛ ላይ የሚመጣብን ተጠያቂነት አይከብድምን?

” ንዑ አራተ ጊዜ ትርአዩ ዘንተ ቅስፈተ አክሊለ ዘሶከ ዘተገብረ ዕጹበ ነገረ ዘተነግረ (ጎር ቁ 40_45) የሚለው ምንባብ የሚያስተምረን፡- ክርስቶስ በለበሰው ሰውነት በመስቀል ላይ የደረሰበትን መከራ ደቂቀ አዳም እንዲመለከተው የቀረበ የግብዣ ጥሪ ነው። ሰለስቱ ምዕት “ገአረ ኢየሱስ ኀበ አቡሁ። . . . . ወሀበ አዳም ገብሩ (ሰለስት 96፣ 99)። ብለው የተናገሩትን አባቶቻችን መነሻ አድርገው፤ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ ለባህርይ አባቱና በምድር ላለው ለደቂቀ አዳም የይግባኝ ድምጽ እንዳሰማ፤ እኛም ህዝባችን ይህን የመሰለ መከራ ሲገጥመው፤ ለዓለም ህዝብ እውልን ስሙልን እያለን እንድናሰማ ነበር።

እንዲህ እንደ ዛሬው የክርስቶስ ተከታዮች ሲታረዱ ሲቃጠሉ፤ ቁስላቸው ግርፋታቸው በዓለም ሁሉ እንዲታይ ማድረግ ነበረብን።

ለዓለም ማሳየታችን ይቅርና፤ ህዝበ ክርስቲያኑ እየታረደ አብያተ ክርስቲያናት እየተቃጠሉ ባሉበት ወቅት፤ ራሳቸው አቃጣዮች አራጆችና ዘር አጥፊወች የተቃጠለውንና የታረደውን ህዝበ ክርስቲያን አረመኔ ሰው የሚያርድ ቤተ ክርስቲያንና መስጊድ የሚያቃጥል እያደረጉ በዓለም መድረክ ሲያቀርቡት ዝም ማለታችን አያስወግዘንምን ?

እግዚአብሔር ሰውን ከራሱ ጋራ ወግኖ በምሳሌውና በአርያው እንደፈጠረው፤ እንስሳትን በየወገናቸው እንደፈጠራቸው የተማርነውን ዘፍ 1፡28 የሰውን ማንነት አበላሽተው ከሰውነቱ ይልቅ እንደ እንስሳ በየቋንቋው ወግነው ሲጨፈጭፉት አትናቴወስ "ህቱ እምውስተ ህዝብክሙ በአበይኖ" ቁ 8። ብሎ ባስተማረን አስተምህሯችን አንጠይቅምን ?

ያዕቆብ ዘሥሩግ የተባለው ኦሮቶዶክሳዊው አባት " ዝኬ ውእቱ ኪደነ ቃልከ ዘታወስአሙ ለካህናት ጼው ለምድር። ብርሃኑ ለዓለም፤ አዕይንተ ቤተ እግዚአብሔር፤ ማህቶተ ቤተ ክርስቲያን "ዘስሩግ 74። ብሎ ቃል ገብተው በክህነት ለተሰለፉት ካህናት እንደተናገረው፡-

ህዝብ ማየት የማይችለውን ከህዝብ የተሰወረውን በቅድሚያ አይታችሁ ለህዝብ እንድታሳዩ የህዝብ ዓይኖች ናችሁ፤ በስውር ያለውን ደባ ለተሰወረበት ህዝብ በመግለጽ እንድታስጠነቅቁ ደወሎች ናችሁ፤ የመረረውን

ህይወት ታጣፍጡ ዘንድ ጨው ናችሁ" የሚለውን በቆረብንባት ወቅት ሁሉ እንደግማታለን።

በዚህ ዘመን ላይ ያለን ካህናት ግን የተሰወረውን በቅድሚያ ልናይ ቀርቶ ለማየት የሚታገለውን ህዝብ እንዳያይ እየሸፈነው ነን። የመረረውን ህይወት ከመጨወት ማለትም ከማጣፈጥ ይልቅ የራሳችንን እሬትና መርዝ እየጨመርንበት ነው። ይህስ አያስጠይቀንምን?

"ክብር ለክሙ ሶበ ትትከሀኑ ምስለ እግዚአ ሰማያት ወምድር " (አት 96 )። " ከሰማይና ከምድር ፈጣሪ ጎን ተሰልፋችሁ ክህነታዊት ተልእኳችሁን ለመፈጸም የምትጥሩ ካህናት ሆይ! ክብር ይገባችኋል " የተባልነው አሁን ባለን ቁመናቸው ነውን? ።

"**ትትከሀኑ**" የምትለውን ቃል መምህሮቻችን እንደኛ እንደዘመኑ ካህናት ከህዝቡ ልዩ ሆነው በሚታዩበት በለበሱት ልብስ ባንገታቸው በእጃቸው ላይ በሚታየው መስቀል ብቻ አይተረጉሙትም ነበር። ይህ አይነት አተረጓጎም ያላቸው፤ ፈሪወች፤ አድር ባዮች፤ አስመሳዮች፤ ህዝበ ክርስቲያኑን የሚያፈዙበት፤ የሚያደነዝዙበትና የሚያቀዙበት ነው ብለው ነግረውን ነበር። ታዲያ እኛ ዛሬ ምንድነን? ምን እያደርግ ነው?

አትናቴወስ "**ትትከሀኑ**" ያለትን ቃል አባቶቻችን ተርጉመው ያስተማሩን *"እስመ ዓዲከሙ ኢጸናእክሙ እስከ ለደም ትበጽሁ ። ተጋደልዋ ለኃጢአት ወእበይዋ ወአብድርዋ ለትምህርተ ተስፋክሙ እስመ ከመ ውሉድ ይብለክሙ ወልድየ ኢታስተጽሕብ ተግሳጸ እግዚአብሔር ወኢትትገሀስ እምኔሁ ሶበ ይዘልፋክሙ"* (ዕብ 12:5) በሚለው ሐዋርያዊ ትውፊት ነው። ይህም ማለት፡- በደለኞችን ግፈኞችን በሰው ላይ የሚፈጽሙትን ግፍ ለማስቆም ገና ደማችሁ እስኪፈስ ድረስ አልተቃ ወማችሁም። እንዲያውም የገባችሁትን ቃል ኪዳን ረስታችሁታል። በሚለው ነው።

ታዲያ ይህችን ጦማር ያነበበ ወገን ምን እያደረጋችሁ ነው ብሎ ቢጠይቀን፤ በራሳችን የደፋነውን ቆብ በደረታችን በእጃች ላይ ያለውን መስቀል የለበስነውን ጥቁር ልብስ በማሳየት *"ሎቱ ንትከሀን ዘውእቱ ክህነት"* አት 149) ብለን ልንመልስለት ነውን? ማለትም የለበስነውን ልብስ የተሸከምነው መስቀል በማሳየት ክህነት ይሉሀል ይህ ነው ልንለው ነውን? ልብሱን መልበስ መስቀሉን መሸከምና መቀደስ ለገንዘብ እንጅ ለመስዋእትነት አይዳርግምና፤ የለበስነው ልብስ የደፋነው ቆብ የክህነትን ሙሉ ትርጉም የሚገልጽ አይደለም።

አባቶቻችን የእግዚአብሔርን ስራ የሚመረምሩባትን **ተባርዮ** የምትለውን ቃል ለማየትና ለህዝብም ለማሳየት በቅተን አልተገኘንም።

ከላይ እንዳልኩት <u>**በተባርዮ**</u> ወቅት፤ ኤጺፋንዮስ "ጠቢብ ውእቱ ዘያሀጉል ምክረ ጠቢባን። ማእምር ውእቱ ዘያረስዕ ህሊናተ መካርያን፤ ኃያል ውእቱ ዘይፈትህ ልጓማተ ጽኑአን፤ ተባዕ ውእቱ ዘያደቅቅ አስናነ ኃጥአን ወይቀጠቅጥ መዝራእተ ዕቡያን " (ኤጺ ቁ 8) ። ብሎ ባስተማረን፤ ማለትም፡- በሰይጣናዊ ጥበባቸው ተነሳስተው ሰው የሚያጠፉበትን የምታፈርስ ፤ ክፉ ምክር የሚመክሩትን ምክራቸውን የምትበትን፤ በትእቢታቸው ንጹሀን ወገኖችን ሲሰብሩ የነበሩትን የጥበበኞችን ጥበብ የምትሰብር አንተ ነህ " እያልን <u>ተባርዮን</u> እያደነቅን በህዝብ ለማስደነቅ ተሰይመን ነበር። እንዲሳለቅበት አደረግነው ።

በዘመናችን የተከሰቱብን የሰው አራዊቶች ከሰውነት የተለዩ መሆናቸውን አስቀድመን አውቀን ለህዝባችን እንድናሳውቅ በቅዱስ አትናቴወስ በኩል "ወኩሎሙ ዐላውያን እለኢየአምኑ በዘተቤዘክሙ ኢኮኑ ደቂቅክሙ አርአያክሙ ወአምሳሊክሙ" (ቅ አትና ቁ 32) ተብሎ ተነግሮን ነበር።

ይህም ማለት፡- ታሪክን ሰባዊ ባህርይን ወገንን አምላክን የሚክዱ የሚከሰቱበት ወቅት አለ። <u>በመልካቸው በቆዳቸው በደም ግባታቸውና በጠቅላላ ቁመናቸው ከእናንተ የተወለዱ ይመስላሉ። ግን በአካላቸው እናንተን ይምሰሉ እንጅ ፈጽሞ ከናንተ የተለዩ አራዊቶች ናቸው የሚል ነው።</u> ከነሱ አራዊታዊ ባህርይ ያለንን ልዩነት ማሳየት ይቅርና በዝምታችን ከነሱ ጋራ ተስማማን።

በዚህ ዘመን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለን ካህናት ወገኖቼ ሆይ ! በዘመናት ውስጥ ያለፉ አባቶቻችን ከነሱ በኋላ የሚከተሉት ካህናት ልጆቻቸው በየዘመናት የሚገጥሟቸውን መከራና ስቃይ የሚሻገሩበትን አስተምህሮ፤ ከብሉያት ከነብያትና ከሐዲሳት ጨምቀው በግልም በማህበርም በምናቀርበው ስርአተ ጸሎት ሰርተው በዝክረ ሊቃውንቱ ቅኔ ቀምረው የሰጡንን ትጥቅ ባለመጠቀማችን እስከዚህች ቅጽበት ድረስ ህዝባችን እያለቀ ነው።

እስካሁን የሞቱትን ወገኖቻችን ልንመልሳቸው አንችልም። ከዚህ በኋላ እንዳይቀጥል፤ ቤተ ክርስቲያናችን የሰጠችንን የዘር ማጥፋት መስፈርት ከአለም መስፈርት ጋራ ደምረን በኛ ላይ የደረሰ በጎረቤት አገሮችና በዓለም አይድረስ ብለን እስክንድር የጀመረውን እነ ሻለቃ ዳዊት በዘር አጥፊወች ላያ ያንቀሳቀሱትን ክስ በገንዘብም በድምጽም በመደገፍ ህዝባችንን እንካሰው።

ቅዱስ ጳውሎስ ፡- "ወእመሰ ዘንተ ገበርከ ታድህን ርእሰከ ወዘሂ ይሰምአከ" (1ኛ ጢሞ 4፡ 16) እንዳለው ይህን ብናደርግ ራሳችንን ከተጠያቂነት፤ የተረፈውን ህዝባችንንም ከቀጣይ ጭፍጨፋ እናተርፋለን።

ተባርዮን የማያስቀር አምላክ የተመሰገን ይሁን !

እንደድሮዎቹ ቄሶች መስለነው ገንዘቡን ለሚያፈሰው ምእመናን ለማስገንዘብ እንጅ፤ ራሳቸው ፓትርያርኩ እንዳሉት በገንዘብ እየገዛ ከተሰበሰበው ከሲኖዶስ አባልና በገንዘብ ክህነቱን በመቸርቸር ላይ ካለው ጳጳስ፤ እየገዛ ከቀሰሰው ከደቆነውና ከቆመሰ ገንዘብ ከመሰብሰብ በቀር ለህዝብ ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር መስዋዕትነት የሚያስከፍል ክህነተዊ ተልእኮ እንደማይጠበቅ ሳልገነዘበው ቀርቼ አይደለም።

በውስጥና በውጭ ያለን ቀሳውስት አባቶቻችን ሰፍረው የሰጡንን የዘር ማጥፋት መስፈርት፤ ዓለም ካዘጋጀው የዘር ማጥፋት መስፈርት ጋራ ደምረን በህዝባችን ላይ ያለውን የዘር ማጥፋት ዘመቻ ለዓለም ባለማሰማታችን ህዝባችንን አልበደለንውምን? የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ካህናት ነን ብለን በህዝቡ ፊት መቆማችን አያሳፍረንምን?

ጀነራል አሳመነው ጽጌ አስቀድመው ተረድተው "እናንት የሃይማኖት አባቶች ሀላፊነታችሁን ተወጡ" እያሉ የተናገሩትን ብንሰማ ኖሮ፤ ከዚያው ወዲህ በመጥፋት ላይ ያለውን ዘር ባተረፍነው ነበር።

ያለበቂ ምክንያት ከቤተ ክርስቲያናችን አጸድ አንዲትን ቅጠል መቁረጥን አጥብቃ በምታወግዘው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናች ውስጥ አለን የምንል ካህናት ወገኖቼ !

ያለፈው በዚህ ሁኔታ አለፈ። እንዲቆም እንዳይቀጥል በኛ የደረሰው ሁሉ ባጎራባች አገሮች እንዳይደርስ አሁን በመን

ቀሳቀስ ላይ ካለው ከነ ኮረኔል ወልደ ጊዮርጊስ ጋራ እንሰለፍ ዘንድ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንችን የምታስተምረውን ዚህ በታች በመግለጽ እደመድማለሁ።

# ለካህናቱ ጥሪ

እከሌ እከሌ ማለቱን እናቁም ! ቤተ ክርስቲያናችን የምትለንን በመከተል ዛሬ በትግራይ ምድር የተከሰተውን ብቻ በጥሰን ዓቢይን ብቻ በመክሰስ ስንጀምር። በመላ ኢትዮጵያ እየተካሄደ ስላለው እንጩህ በንከኪ የጠፋውን በሁለንተናው የጠፋውን ዘር ገለልተኛ የሆነ አካል ይመልከተው ብንል ማን አጥፊና ማን ጠፊ እንደሆነ ለሱ እንተወው። እኛ ግን ከዚህ የሚከተለውን ተግባር ለመፈጸም እንሞክር